# በኢህአዴግ ሜዳ ላይ "አውራጅና ጫኝ" ለምን በዛ?

*አጩሌ (የአሜሪካ ግቢው - ከኢህአዴግ ሜዳ) 02-28-18*

መርህ ባቆመውና እንደ አዲስ በሰራው ድርጅት ውስጥ መርህ አልባነት መንገዳገድ ካልፈጠረ በቀር በመርህ ላይ የተመሰረተውንና በመርህ የተፈጠረውን ድርጅት ጨርሶ አያጠፋውም። ለዚህም ነው ኢህአዴግ ጠፋ ሲባል ህልው ሆኖ እንደ አዲስ የሚፈካው፤ ራሱን አድሶም የሚወጣው።

በአገራችንና መንግስትን በሚመራው ድርጅት ውስጥ ከዚህ ቀደም ያጋጠሙ መፍረክረኮች ያልነበሩ ያህል ተወግደው እንደ አዲስ መጓዝና በብጥብጥና ትርምስ በተሞላው ጂኦፖለቲካዊ ሁኔታ ውስጥ የአገራችን ሰላም ተጠብቆ መጓዝ መቻላችን ይህን ያመላክታል።

ብዙዎቹ ጎረቤት አገራት በሽብር፣ እርስ በእርስ ብጥብጥና ጦርነት በተጠመዱበት ባለፉት 20 ዓመታት ከራሳችን አልፈን ለሌላው ሰላም አስተዋፅኦ ማድረግ የቻልነው፣ ታላቅ አገርና ህዝብ የመገንባት ስራችንን በስኬት ይዘን የተጓዝነው፣ የዓለም አይኖች በዲፕሎማሲም፣ በኢኮኖሚያዊ ተሳትፎም አገራችን ላይ እንዲያነጣጥሩ ለማድረግ የበቃነው ህዝባዊና ህገመንግስታዊ መርሃችንን ይዘን በመዝለቃችን ነው።

አሁን ያለው መርህ የመረው ድርጅት ብቻ ሳይሆን ህዝቡ የመረጠው፣ ይዞት የቀጠለው፣ ይዞትም የሚዘልቀው የህዝብ መስመር መሆኑን በደረስንበት እድገት፣ ባለቤት ሆኖ እየፈፀመው ባለው ተዋናይ፣ መርህ መሳትና መጣረስ ሲመጣም የመረጠውን መንግስት እየጠየቀና እያስገደደው ባለው ህዝብ ህጋዊና ሰላማዊ ትግል ማየት ይቻላል።

ከዚህም አኳያ ምንም ያህል የመርህ መጣረስና ወጣገባነት ቢከሰት ወደቀደመው ለመመለስ ጊዜ ይጠይቅ ይሆን እንጂ ህዝቡ ባለቤት የሆነበት መስመርና መርህ በህዝቡና በድርጅቱ እርማት እየተደረገበት መጓዙ አይቀርም። ይህን ሰላማዊ የእርማት አካሄድና አቅጣጫ በመጠምዘዝ፣ ህዝቡን ስጋት ውስጥ በመጣልና በማጨናነቅ ወዳልተገባ ህገወጥ አቅጣጫ ይዞ የመዝለቁ የጥቂቶች ፍላጎትና እሳቤ የቱንም ያህል ቢሞከር መላተሙ ይዞት የሚመጣው ጉዳት በንፁሃን ዜጎች ላይ የሚያስከትለው ዘግናኝ ጥፋት ያስቆጭና ያንገበግብ ካልሆነ በቀር የብዙሃኑን ፍላጎት የሚቀለብስ አይሆንም።

ይልቁንም መንግስት የዜጎች ሰላም እንዳይታወክ ኃላፊነቱን ይበልጥ እንዲወጣ ህዝቡ በመንግስት ላይ ጫና ያሳድር እንዲሁም ከመንግስት ጋር ተባብሮ ለሰላሙ ይበልጥ ሊታገል ካልሆነ በቀር የሰላሙንና የህልውናውን ዋስትና ለአደጋ ጣዮች አሳልፎ አይሰጥም። በተጨባጭ እየታየ ያለው የመሻሻል፣ የመደማመጥና በስክነት የመወያየት ሂደት ይህን የሚያሳይ ነው።

በእርግጥ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ በህዝቡም ይሁን በተለያዩ አደረጃጀቶች፣ መንግስትን እየመራ ባለው ግንባር ውስጥ ያሉ ብሄራዊ ድርጅቶች ባቀረቡት ፕሮግራም ላይ ተመስርቶ የመረጣቸው ህዝብ፣ የፓርቲዎቹ ክልላዊና አገራዊ ቁመናና ምግባር ባሰመሩት መስመርና መርህ ላይ ሆኖ እየተጓዘ ነው ወይ የሚል ጥያቄና ግርታን ፈጥሯል።

በሌላ አገላለፅ ብሄራዊ ድርጅቶቹ በየክልሎቻቸውና እንደ አገር በዴሞክራሲያዊ አንድነት ተሳስረው፣ ለብዙሃኑ ባላቸው ውግንናና መስመር ላይ ተመስርተው የሚፈፅሟቸው ተግባራት እንዴት ባለ አንድነትና መተባበር እየተጓዘ ነው የሚለው በኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ዝርዝር ግምገማ ከተደረገ በኋላ በየብሄራዊ ድርጅቶቹ ሊቃነመናብርት በኩል ማብራሪያ ቢሰጥበትም፣ ከዚያ በኋላ ባለው ሂደት የሚታዩ ያልታረሙ (አንዳንዶቹ ህዝቡና ኢህአዴግ ጊዜ ወስደው በቀጣይ ሊያዩአቸው የሚገቡ) ወጣ ገባዎች አሁንም በህዝቡ ውስጥ የሚስተዋለውን ጥርጣሬ ያላፀዱ ናቸው።

ይህ ጥርጣሬ አራቱ የኢህአዴግ ብሄራዊ ድርጅቶች ካሉባቸው ክልሎች ባለፈ በሌሎች ክልሎች ባሉ ህዝቦችና ህዝቡን በሚያስተዳድሩት አጋር መንግስታትና ህዝቦችም ዘንድ ግርታን ፈጥሯል። አገሪቷ ኢህአዴግ በህዝብ ከተመረጠባቸው ክልሎች ባለፈ አጋር ድርጅቶችና መንግስታት የሚመሯቸው ክልሎች ህዝቦችም ጭምር በመሆኗ አጋር ድርጅቶችም ሆኑ ህዝቡ ኢህአዴግ በተመረጠበት መስመርና መርህ እንዲጓዝ የማስገደድ መብት እንዳላቸው መረዳትም ያስፈልጋል። ሌሎች ክልሎችን እንዲመሩ የየክልሎቻቸው ህዝቦች የመረጧቸው አጋር ድርጅቶች ከኢህአዴግ ጋር እየሰሩና በጋራ እየተጓዙ ያሉት የኢህአዴግ ፕሮግራምና መስመር እንዲሁም መርህ ላይ ተመስርተው በመሆኑ በኢህአዴግ ውስጥ ያሉ ብሄራዊ ድርጅቶች ይህንኑ ጠብቀው እንዲጓዙ ማስገደድም ይችላሉ።

በኢህአዴግም ውስጥ ያሉ ብሄራዊ ድርጅቶችም ህልውናቸው የተወዳደሩበትን ፕሮግራም አምኖ በመረጣቸው ህዝብና እንዲመረጡ ባደረጋቸው ድርጅት ላይ መመስረቱን አውቀውና የመሪነት ስልጣን ያገኙትም በድርጅታቸው ፕሮግራም መሆኑን ተገንዝበው በዚህ ዙሪያ ያላቸውን ብዥታ በፍጥነት

ሊያስወግዱት ግድ ይላል። ከዚህ አኳያም መርህን ስቶ አብሮ የማዘመር ሳይሆን፣ መርህ ላይ ተመስርቶ ህዝብን ለሰላም፣ ለተሻለ መልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ፣ ለተሻለ ልማትና የጋራ ተጠቃሚነት የማሰለፍ አጀንዳን ማስቀደም ይኖርባቸዋል። ይህ በሌለበት የእነሱ አካላዊ ህልውና ብዥታው ሲጠራ ተጠያቂ ያደርጋቸው ካልሆነ በቀር የተጀመረውን አገራዊ ሁለንተናዊ ጉዞ ፈቅ የሚያደርገው አይሆንም።

ከነባራዊ አገራዊ ሁኔታዎቹ በጥልቅ መረዳት እንደሚቻለው በአሁኑ ወቅት የአገራችን ህዝቦች በቀዳሚነት የሰላም እጦት ስጋት ውስጥ ገብተዋል። በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች ከሰላማዊ ትግል ያፈነገጡና በማንነትና ዘር ላይ ያተኮሩ ወጣቱንና ህዝቡን ሽፋን አድርገው የተፈፀሙ ዘግናኝ ጥቃቶች የብዙ ሰላማዊ ዜጎቻችንን ህይወት ቀጥፈዋል። ህገመንግስታዊ የመዘዋወርና ሀብት የማፍራት መብትን ተፃርረው በዜጎች ላይ የንብረት ውድመትና የአገር ኢኮኖሚ ክስረትን አድርሰዋል።

የአገራችን ሰላም አስተማማኝ መሆኑን ተረድተው ራሳቸውን ጠቅመው ዜጎቻችንን እየጠቀሙ ያሉ የውጭ ባለሃብቶች ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችን በማዳከምና በማጥፋት የአልሚዎቹን ተስፋ ከመንጠቅ ባለፈ የዜጎቻችንን የዕለት ተዕለት ህይወትና የማደግና የመለወጥ ተስፋ አዳምነዋል። ሌሎች የውጭ አልሚዎች ብቻ ሳይሆኑ ሀብትና ንብረታቸውን በአገራቸው ማዋል የሚፈልጉ ዜጎቻችን ጭምር መስራትና በየአካባቢው ያለውን ወጣት መጥቀም እንዳይችሉም አድረገዋል። በሌላ አነጋገር አንዳንድ በመልማት ፍላጎት ስም የሚነሱ የሀይል ጥያቄዎች የፍትሃዊ መልማት ጥያቄን በራሳቸው ሲያዳፍኑና ሲያዳክሙ ተስተውለዋል። ከዚህም አኳያ እየተስፋፋ ያለውን ጥፋትና ውድመት በህብረተሰቡ የጋራ ተሳትፎ በማስቆም መላው ህዝባችንን  ከስጋት ነፃ ማድረግ፣ የነበረውን ሰላም መልሶ ማረጋገጥ ቀዳሚ ሆኖ ይታያል።

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ የተገመገመውን ዝርዝር የሰላምና ፀጥታ ጉዳይ፣ በተቋቋመው የፀጥታና ደህንነት ምክር ቤት የተደረሰበትን ድምዳሜ እንዲሁም በዋናነት ህዝቡ ውስጥ ያለውን ተጨባጭ ስጋት ግምት ውስጥ በማስገባት ረፍት ላይ ያለው ምክር ቤት ወደ ስራ እስኪመለስ ለ15 ቀናት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማወጁ ለዚሁ ነው። አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ለ6 ወራት እንዲቆይ በምክር ቤቱ መፅደቁም በአመፅና ብጥብጥ ዘርና ማንነትን እየለዩ የዜጎችን ህይወት አደጋ ላይ የጣሉ ወንጀለኞች በህግ እንዲጠየቁ የሚያስችለውን መደበኛ አሰራር ከማስፈን ባለፈ፣ የህግ የበላይነትን

በማክሰም ስርዓት አልበኝነትን ለማንገስ የሚሯሯጡ ህገወጦችን ህዝቡ ራሱ እንዲያጋልጣቸውና በህግ ተጠያቂ እንዲያደርጋቸው እድል ይሰጣል።

አሁን ባለው ሁኔታ በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች ባሉ የክልልና ዞን እንዲሁም ወረዳ አስተዳደርና ፀጥታ ማዕከላት ወጣቱን በማደናገርና በማስፈራራት ጭምር ላልተገባ ጥፋት አሰልፈው በአስፈፃሚው ላይ ጭምር የህይወት መጥፋትና አካል ማጉደል ርምጃ እየወሰዱ ያሉ ወንጀለኞች ሽፋናቸው ዘርና ማንነት ቢሆንም ድርጊታቸውን ያወገዙትን ብሄርና ማንነት ሳይለዩ ጭምር ግድያ መፈፀማቸው ተግባራቸው ለማንም ያልወገነ ሽብር ማንገስ መሆኑን ያመላክታል። ስለሆነም አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን በመቃወም ጭምር የሚፈፅሙት የጥፋት ተግባር የራሱን የወጣቱን በሰላም የመኖርና የመስራት ህገመንግስታዊ መብት ጭምር በመጋፋት አካባቢን ለጥፋትና ለከፋ ድህነት የሚዳርግ በመሆኑ በራሱ በወጣቱና በየአካባቢው ህዝብ መወገዝ ይኖርበታል።

ለአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ሌላ ቅጥያና ስም በመስጠት በህዝቡና ወጣቱ ውስጥ የሚፈጥሩት መደናገርም እያንዳንዱን ክልል የሚመራው መንግስትና ፓርቲ በህዝቡ ውስጥ ግልፅነት በመፍጠር ህዝቡ ራሱ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ባለቤት ሆኖ በመስራትና አስተማማኝ ሰላም በመፍጠር አዋጅ የማያስፈልግበት ደረጃ ላይ ማድረስ ይኖርበታል።

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ስራ ላይ እንዳይውል ማድረግም ሆነ የህግ አስከባሪውን ስራ ማወክ በአስቸኳይ ጊዜ ኮማንድ ፖስት የእርምጃ አፈፃፀም መመሪያ 01/2010 ክልከላ የተደረገበት መሆኑ ግልፅ ሆኖ ሳለ፣ የህግ የበላይነትንና የህዝብ ሰላምን ለማረጋገጥ የወጣ መመሪያ በመጣስ ለሌላ ብጥብጥና ጥፋት ወጣቱን ለማሰማራት የሚደረገው እንቅስቃሴ ጨርሶ አልጠፋም። በዚህም ምክንያት ኮማንድ ፖስቱ ህገወጥ ሀይሎች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ በድጋሚ አስጠንቅቋል።

በተለይ መንግስትን የሚመራው ኢህአዴግ የህዝቡን የተለያዩ ፍላጎቶችና ጥያቄዎች እንዲሁም ቀጣይ አገራዊ ፍላጎቶችን ታሳቢ በማድረግ በስክነትና በትዕግስት ረጅም ጊዜ ወስዶ በመወያየት የወሰዳቸውን ተከታታይ ርምጃዎች፣ በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ውስጥ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የተደረጉ ጥልቅ ውይይቶችና ማሻሻያ ሃሳቦች፣ የስልጣን አተያይ ላይ ግላዊነተ የድርጅቱ ዋና ችግር ነው ብሎ በመገምገም ይህን ችግር ፈር ቀዳጅና አርአያነት ባለው መልኩ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የራስና የፓርቲ ፍላጎት የተወሰደ

ርምጃ ወዘተ... የእነሱ ትግል እንዳመጣው አድርገው የባለቤትነት መብት ለማስመዝገብ የሚቃጣቸው ወገኖች አስገራሚና አስደማሚ እንቅስቃሴዎችንም መታዘብ ተችሏል።

እነዚህ ወገኖች አብዛኞቹ ስለኢህአዴግ ባህልና ውስጥ አሰራር የማያውቁ፣ ይልቁንም ኢህአዴግን በጭፍን በመክሰስና በጭፍን በመቃወም የሚታወቁ ሲሆኑ የድርጅቱን የእርስ በእርስ ግምገማና የሃሳብ ፍልሚያ መበተንና መከፋፈል አድርገው ወስደው እንደ ኢህአዴግ አባል ኢህአዴግ ሆነው ሲሾሙና ሲጥሉ ይታያሉ። በምርጫ አሸንፎ በወጣው ፓርቲ ውስጥ ስልጣን በድርጅታዊ ብቃት ላይ በመመስረት አገራዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚን አሸናፊ አድርጎ በመዝለቅ፣ ድርጅቱ በተመረጠበት ፕሮግራምና መስመር እይታ አገርንና አካባቢን የመምራት ጥበብ መጎናፀፍ ላይ በመመስረት የሚደረግ መሆኑን መረዳት ተስኗቸው በግል ፍላጎት ላይ ተመስርተው አያገባቸው ገብተው ሲተነትኑና በጭፍን በሚጠሉት ኢህአዴግ ላይ ተንታኝና አቅጣጫ ሰጪ ሆነውም ይስተዋላሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ለምናልባቱ ይሄ ስርዓት ቢፈርስ እንጠቀም ይሆናል ብለውና ባላዘጋጁት ፓርቲ ህልም ውስጥ ገብተው በጭፍንና ያለ ምክንያት ሲተቹ ይስተዋላሉ።

ሁለቱንም ወገኖች አንድ የሚያደርገው ግን በስልጣን ላይ ያላቸው አተያይ ነው። ቀረብ ሲል ደግሞ የጠቅላይ ሚኒስትርነት ቦታን የግል ስልጣንና የጥቅም ማስጠበቂያ አድርገው ማየታቸው ነው። ይህን ተንተን አድርጎ ለማየት፣ እነዚህ ወገኖች የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤቶች የኢትዮጵያ ህዝቦች መሆናቸውን አያውቁም። ጠቅላይ ሚኒስትሩ የስልጣን መልቀቂያ አቅርቤያለሁ ሲሉ እንደ አገርና ፓርቲ የቻልኩትን ያህል ሰርቻለሁ፤ ነገር ግን በአገሪቱ በተከሰተው ችግር ለህዝቤ ማድረግ ያለብኝን አልፈፀምኩም። ከእኔ ይልቅ ችግሩን ለመፍታት ሌሎች ይስሩ ማለታቸውን አይገነዘቡም። በሌላ አነጋገር የያዝኩት ወንበር ፓርቲዬን የመረጠው ህዝብና ፓርቲዬን ያልመረጠው ህዝብ ጭምር ነው የማለታቸውን ትህትና አይረዱም።

ለእነዚህ ወገኖች የስልጣን ባለቤት ሉዓላዊው ህዝብ ስላይደለ የአሜሪካን ኤምባሲን ወይም የጀርመን መንግስትን ወይም የእንግሊዝ መንግስትን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተቃውሞ በማጉላት የሰላም እጦት ስጋት የገባውን ህዝብ ፍላጎት ሊጨፈልቁ ይሞክራሉ። የስልጣን መልቀቂያው ወደ ስርዓት ለውጥ እንዲያመራ በጥልቅ በመመኘትም የእነሱ ፍላጎት የህዝብ ፍላጎት እንደሆነ አድርገው ይገልፃሉ፤ ፍላጎቱ የውጭ መንግስታት ፍላጎት መሆኑንም ያወሳሉ።

ስለዚህም በማያውቁት የድርጅት ጉዳይ ገብተው የህልማቸውን መሻት ይሰቅላሉ፣ ያወርዳሉ። በእነሱ ያልተገባ ቅስቀሳ ተነሳስቶ በንፁሃን ላይ እርምጃ በሚወስደው ወጣትና ራሱንም ጭምር እሳት ውስጥ ለሚጨምረው ወጣት ቅንጣት ሰብዓዊነት ሳይሰማቸው ለጥልቁ የአመፅ ምኞታቸው ስኬት ሲሉ የብሄር እሳት ሲያቀጣጥሉ ውለው ያድራሉ።

ከስልጣን አተያይ አንፃር ስልጣንን ህዝብን ለማገልገል ሳይሆን ራስን ለመጥቀም ማየት በድርጅቴ በስፋት ታይቷል፣ ተገምግሟል ሲል የቆየው ኢህአዴግ ይህን ባህል መስበር መጀመሩን በጠቅላይ ሚኒስትሩ የስልጣን መልቀቂያ ጥያቄ ብቻም አይደለም የጀመረው።

ከኢህአዴግ አራት ድርጅቶች ግምገማውን በቀዳሚነት የጀመረው ህወሓት ሊቀመንበሩን ጨምሮ 4 የስራ አስፈፃሚ አባላቱን በጥልቅ ገምግሞ አንስቷል። ማዕከላዊ ኮሚቴው ላይ ጭምር ችግር አለበት ያለው አመራሩን በማንሳት ሌላም ካለ በዝርዝር እያየሁ እቀጥላለሁ ብሏል።

ኦህዴድም ራሱን በጥልቅ በመገምገምና ውስጡን በመፈተሽ ከቀደመው ጥልቅ ተሃድሶ ጀምሮ በማዕከላዊ ኮሚቴው ውስጥ አሉ በተባሉ ችግሮች ተጠያቂ ያላቸውን ከቦታ አንስቷል። ግምገማውንም በክልሉ አንዳንድ አካባቢዎች ያሉ ችግሮች ሳይገድቡት ወደ ታች አውርዷል።

ብአዴን በስራ አስፈፃሚና በማዕከላዊ ኮሚቴው አፈፃፀም አሉ ያላቸውን ችግሮች በመፈተሽ ከቀደመው ጥልቅ ተሃድሶ ጀምሮ ባደረገው ግምገማ ችግር አለባቸው ያላቸውን ሁለት የማዕከላዊ ኮሚቴ አመራሮች ከድርጅት ቦታ ማንሳቱና ራሱን በጥልቀት እያየ መጓዙም ይታወቃል።

የደኢህዴን ስራ አስፈፃሚም የሊቀመንበሩ አገራዊና ድርጅታዊ አስተዋፅኦ ከፍታ ለአገሪቱም ለአህጉሪቱም የተበረከተ ድርጅታዊ ተልዕኮ መኖሩን እያወቀ የሊቀመንበሩን የስልጣን መልቀቂያ ጥያቄ በመቀበልና ድርጅታዊ አርአያነቱን በማደነቅ ራሱን በጥልቅ እያየ መጓዙን አመላክቷል፣ ይህም እስከ ታች እንደሚቀጥል አሳውቋል።

ስለሆነም የአቶ ኃይለማርያም የስልጣን መልቀቅ ጥያቄ አገራዊ ኃላፊነትን እና የኢህአዴግ ሊቀመንበርነትን ታሳቢ ያደረገ ከመሆኑ አኳያ ካልታየ በስተቀር የኢህአዴግ ሪፎርም በራሱ በኢህአዴግ የተፈፀመና እየተፈፀመ ያለ እንጂ የኢህአዴግን ሪፎርም ሃሳብና የህዝብን የላቀ ተጠቃሚነት እይታ ጠልፈው የራሳቸው ለማድረግ በሚሞክሩ ወይም በውጭ ሀይሎች ግፊት የመጣና የሚመጣ አይደለም።

ይልቁንም የኢህአዴግ ሪፎርም በአባል ድርጅቶቹ ራስን በጥልቅ የማየት ጅማሬ የተጓዘ፣ ወደ ግምገማ ከመግባቱም በፊት በአራቱ የድርጅቱ ሊቃነመናብርት የጋራ አቅጣጫ የተቀመጠበት፣ በዚሁ መሰረት በየብሄራዊ ድርጅቱ ራስን የመፈተሽ ተግባር የተፈፀመበት ሲሆን፣ በዚህ ሂደት በድርጅቶቹ ውስጥ እየተስተዋሉ ያሉ ወጣ ገባዎችም መፍትሄ ራሳቸው ድርጅቶቹ መሆናቸውን በግላጭ ያየንበት ነው።

ነገር ግን አሁንም ቢሆን ኢህአዴግ በእኔ ሜዳ ላይ አውራጅና ጫኙ ለምን በዝተው ታዩ? ብሎ በማያዳግም ሁኔታ መፈተሽ አለበት። ከጥልቅ ተሃድሶ ጀምሮ በጥልቅ እየገመገመ ያለው ኢህአዴግ የጎራ መደበላለቁ ሰፊ መሆኑን በተገቢው ለይቷል፤ ህዝበኝነቱ የት ድረስ እየተጓዘ መሆኑንም በጥልቀት ገምግሟል። እና ምን እርምጃ ወሰደ ብሎ በድፍረት ለመናገር ኢህአዴግ ጊዜም ነበረው፣ ጊዜም አልነበረውም።

አሁንም በእርግጠኝነት ጊዜ አለው፤ ጊዜም የለውም። እናም በጊዜ የለኝም መንፈስ ኢህአዴግና አራቱ ድርጅቶቹ መርህ አልባዎቹንና ህገወጦቹን አውራጅና ጫኞች ከሜዳው አስወጥቶ የጀመረውን ጉዞ ይቀጥል። አጋር ድርጅቶችም በመተማመን ላይ ተመስርተው ከኢህአዴግ ጋር ይራመዱ።